# "ወሬ ቢነግሩት ሃሳብ ጨመረበት" አለ ባላገር

**ዮናስ**

አለማችን ዛሬ አንድ መንደር ሆናለች፡፡ ስለመሆኗም ማሳያ ፍለጋ ብዙ ርቀት መሄድ ሳያሻን ኑሮአችንን ብቻ በመመልከት ማረጋገጥ ይቻለናል፡፡

ይህም ማለት ልክ እንደተፈጥሮ  ከባቢያችን አንዱ ስለአንዱ መኖርና ያለመኖር ወሣኝ ነው ማለት ነው፡፡ ኋላ ቀር በነበረችው የድሮዋ አለማችንም ቢሆን ግንኙነቱ በአካባቢያችን የተገደበ መሆኑ እንጂ ሰው ለሰው መድሃኒቱ ነው እንዳሉ በግል በሚኖረን ህይወትና ከክልል ክልል በሚኖሩን ማናቸውም የሰው ለሰው ግንኙነቶች ውስጥ አንዱ ለአንዱ ግብዓትና ትርጉም ያለው ሆኖ ታይቷል፡፡ ዛሬ የምንገኝባት ዓለም ደግሞ ሚዛኗን ጠብቃ ለመጓዝ ከሰው ለሰው አልፋ የሃገራትን እና አህጉራቱን ግንኙነት የግድ ትሻለች፡፡ ዓለማችን በማህበረ ኢኮኖሚና ፖለቲካው መስክ ከሰው ልጆች እድገትና ፍላጎት ጋር ተያይዞ እውነትም አንድ መንደር ሆናለች ተብሎ ቢነገር የተጋነነ አይሆንም፡፡ በዚህ የማህበረ ኢኮኖሚና ፖለቲካዊ የሃገራት ትስስሮሽ ውስጥ ደግሞ በርካታና ሥፍር ቁጥር የሌላቸው ጉዳዮች ሚና ቢኖራቸውም በግሌ የሚዲያ ሚና ግን ከሁሉም የሚጎላ ይመስለኛል፡፡

ሀገራችን እንደ ሀገር ከምትከተለው ሥርዓተ መንግሥትና የውጭ ግንኙነቷ ጋር የዓለማችን አንድ አካል እንደመሆኗና በተለይም አሁን ካለችበት የሥልጣን ሽግግር ጋር ተያይዞ   ሰፊ የሚዲያ  ሽፋን እየተሰጣት ይገኛል፡፡

በዚህ ጽሁፍ ላወሳ  የፈለግሁት አሁን ያለውን የሀገሬ ፖለቲካ ተከትሎ ምን እየተባለ ነው? ከሚለው በመነሳት ሚዲያውንና ጋዜጠኝነትን ከመርህና ከፕሮፌሽናሊዝም አንፃር ምሣሌዎች እያነሳሁ በመፈተሽ የውይይት መንገድ ማመቻቸት ነው፡፡

ሚዲያ መንገዱ ነው፡፡ ጋዜጠኝነት  ደግሞ እውቀት ነው፡፡ ጋዜጠኝነት ሙያ ነው፡፡ ጋዜጠኝነት ሚዛናዊነት ነው፡፡ ጋዜጠኝነት ተሰጥኦና ፍላጎትም ነው፡፡ ጋዜጠኝነት ኃላፊነት መሸከም ነው፡፡ ጋዜጠኝነት አርቆ አሳቢነት ነው፡፡ ጋዜጠኝነት እናት፣ አባት፣ ወንድም፣ እህት፣ ልጅ፣ መስራት፣ መነሳሳት ሁሉን የመሆን ጥበብ ነው፡፡

ከጋዜጣ ህትመት ጋር ተያይዞ ጋዜጠኝነት ወደፕሮፌሽናል ደረጃነት ከተሸጋገረ ጀምሮ ዛሬ ያለበት ደረጃ ሲፈተሽ ጉዞው የኋሊት ወይም መርህ የለሽና አፈንጋጭ ሙያ እየሆነ የመጣበት ሁኔታ እንዳለ የሚያመላክቱ በርካታ ነገሮች እየተስተዋሉ ነው፡፡

ጋዜጠኝነት ሲወሳ  በነፃ ማሰብና መፃፍ፣ ሀሳብን በነፃነት ከመግለጽና መረጃን ከማግኘት መብቶች ጋር ተያይዞ የሚነሳና በዚሁ ማዕቀፍ ውስጥ ሲከናወን ብቻ ነው ስለ ፕሮፌሽናሊዝም መነጋገር የሚቻለው፡፡ እንደየሀገረ መንግሥታቱ ሥርዓተ መዋቅር እና እንደሚከተሉት ርዕዮት ሙያውና ሚዲያው የራሳቸው

ውስንነቶች ቢኖሯቸውም ጋዜጠኝነትን ከፕሮፌሽናሊዝም አንፃር ስናነሳ መረጃ የማግኘት እና የመፃፍ ነጻነት ግን በየትኛውም መልኩ ይዘነጋሉ ብዬ አላስብም፡፡

ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አማራጭ የሌለውና የሁሉም ሀገራት የመጨረሻ ግብ ሆኖ በተቀመጠበት አግባብ ሚዲያና ጋዜጠኝነት የዓለማችን አልሚና አጥፊ እስከመሆን የደረሱበትና የሚችሉበት ሁኔታ ላይ ደርሰናል፡፡

የምፅፈው ስለሀገሬ ሰሞንኛ ፖለቲካ ነው፡፡ እንድንነጋገር የምፈልገውም ስለገዥ ሥርዓቱና ስለኢህአዴግ ነው፡፡ ጉዳዩ ስለኢህአዴግ ሚዲያው ምን እያለ ነው? ምንስ እያሰራጨ ነው? ፀሐፊዎቹና ማሰራጫዎቹ ከኢትዮጵያ ጋር ያላቸው ግንኙነትና ፍላጎትስ ምንድነው? የሚሉ ጥያቄዎችም አሉኝ፡፡

እነዚህ ፀሐፊዎች በግልና እንደተቃውሞ ጎራ ግንባሩንና ብሄራዊ የሆኑትን ድርጅቶች እስከምን ድረስ ያውቋቸዋልና ነው በላይ በላዩ መአቱን እያወረዱና እያሟረቱ የሚገኙት? እነዚህና መሰል አጀንዳዎችም ዋናና የፅሁፌ መዘወሪያዎች ይሆናሉ፡፡ እነዚህን አጀንዳዎች ለመፈተሽ ደግሞ በጥቂቱም ቢሆን ፕሮፌሽናል ስለሆነው የጋዜጠኝነት መርሆዎች እና ፈተናውን ማንሳት ጠቃሚ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡

ከጋዜጠኝነትና ሚዲያ ጋር ተያይዞ የፕሮፌሽናሊዝም ፍልስፍና አባት የህትመት ሚዲያው ቢሆንም ዛሬ የደረስንባቸው በርካታ ሚዲያዎችም ሆኑ ጋዜጠኝነቱ መርሃቸው ያው ከህትመት ሚዲያው ጋር አብሮ የተፈጠረው ፕሮፌሽናሊዝም እንደሆነ ብዙዎቹና በመስኩ ላይ ምርምር ያደረጉ ባለሙያዎች ያረጋግጣሉ፡፡

የፕሮፌሽናል ጋዜጠኝነት ጽንሰ ሀሳብ በሚዲያ ኢንዱስትሪው ውስጥ የሚስተናገዱ ሀሳቦች የሚዲያ ባለቤቱ ሀሳቦች ሳይሆኑ ሙያቸውን ጋዜጠኝነት ብቻ በማድረግ ነባራዊውን እውነት በገለልተኝነትና በትክክለኛነት እንዲሁም በፍትሃዊነት መስፈርት በማንፀባረቅ በሀሳብ ግብይት ሂደቱ ለመሳተፍ የመረጡ ሙያተኞች አስተሳሰቦች ወይም የምርምር ውጤቶች እንደሆኑ አስመስሎ ማቅረብ ነው፡፡ ስለዚህም ተጨባጭነት፣ ገለልተኝነት እና ፍትሃዊነት የሙያው መለያዎች እንደሆኑ ፕሮፌሽናሊዝም ጥቅም ላይ መዋል ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ በተግባር የዋሉ መስፈርቶች እንደሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ስለሆነም ተጨባጭነትን፣ ገለልተኝነትንና ፍትሃዊነትን የጽሁፌ ማጠንጠኛ በማድረግ ሰሞነኛውን የሀገሬ ፖለቲካ እና የሥልጣን ሽግግር የተመለከቱ ዘገባዎች ፈትሻለሁ፡፡

ተስፋዬ ገብረአብን መቼም ለአቅመ ንባብ የደረሰ ሁሉ ይስተዋል ብዬ አላስብም፡፡ ቀደም ብሎ በነበሩት ሥራዎቹ ምን አስተላልፎልን እንደነበርና ሥራዎቹም ምን ላይ ትኩረት አድርገው የቀረቡ፣ ዓላማቸውና ግባቸውም ጭምር ምን እንደነበር ለበርካታ ጊዜ በተለያዩ ጋዜጦች ላይ ተጽፏል፡፡ ለክርክርና ውይይትም ቀርቦ ወደ አንድና ሁሉንም የሚያስማማ መደምደሚያ ላይም ተደርሷል ብዬ እገምታለሁ፡፡

“በቡርቃ ዝምታው” የብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦችን ሠላምና በመከባበር ላይ የተመሰረተ አንድነት ለማደፍረስ ሲል የቡርቃን ወንዝ በከለ፤ በቢሾፍቱ ቆሪጦቹም ቆራጣ ሀሳቡን ደሰኮረ፤ በጋዜጠኛ ማስታወሻው ደግሞ የግለሰቦችን የግል ጉዳይ ወተወተ አሁን ደግሞ የመለስን ሞት እንደ ሞተር መቀስቀሻ ተጠቅሞ ብቅ ብሏል፡፡

ሰይጣናዊ መልዕክቶቹን እና ተጨባጭ ያልሆኑ ወሬዎቹን የሚያስተላልፈው ደግሞ በኒዮ ሊበራሉ ሚዲያዎች በኩል ነው፡፡ በሴፕቴምበር 2012 ላይ "ዣንጥላው ተቀደደ" ሲል በድረ ገጽ በለቀቀው ዲስኩር ደርሶ የፖለቲካ አማካሪ ሆኗል፡፡ የአራጋቢነት ሚናውንም ተወጥቷል፡፡ ልክ እንደ እርጎ ዝንብ በማይጠበቁና በህልምም እንኳ ቢሆን ይመለከተዋል ብለን ካላሰብነው ቦታ ሁሉ ጥልቅ ብሏል፡፡ የኢፌዴሪን የመንግሥት ካብኔ በእርሱ አጋፋሪነትና ምክርም ይዋቀር ዘንድ ሽቷል፡፡

በእርግጥ የተስፋዬ ሀሳብና ዲስኩሮቹ ሁሉ ለመታመን ያልቀረቡ፣ ተጨባጭ ያልሆኑና ከፍትሃዊነት ጋር ፍፁም የማይተዋወቁ በመሆናቸው መቼም ቢሆን ግባቸውን መተው አያውቁም፡፡ "ዣንጥላው ተቀደደ" ም የገጠመው ዕጣ ፈንታ ይኸው "እንቶ ፈንቶ" የሚል ነቀፋና ለበጣ ነው፡፡

የሚገርመው ደግሞ ተስፋዬና መሰሎቹ ከገቡበት ስህተት መውጣት አይፈልጉም፤ አይሞክሩትምም። ይልቁንም ለምን ተነቃብኝ በሚል ግብታዊነት ወደሌላ ስህተት በተደጋጋሚ ያመራሉ፡፡ "ዣንጥላው ተቀደደ" ሲከሽፍ ተስፋዬ ያመራው ወደ "ኃይለማርያም አንገት" ነው፡፡

በኃይለማርያም አንገት ማስተላለፍ የፈለገው ሀሳብም ያው የተለመደውን የጎሳ ፖለቲካ እና የብሔሮችና ብሔረሰቦችን ሽኩቻ መሻቱን ነው፡፡ የህወኃትን ሲቪል እና የመከላከያ አባላት ተስፋዬ የእናቱን ያህል ያውቃቸው ይመስል ስለሥልጣን ሽግግሩ ያላቸው ምልከታ ቀና አይደለም ሲል ደምድሞ ይናገራል፡፡ በቀና አላማየታቸው ደግሞ እውነትም ነው፤ ተገቢም ነው ሲል ያልበላውን ያካል፡፡ ያን ታምራት ገለታንም ይሆናል ተስፋዬ፡፡ "ከሰሞኑ በተፈጠረው ሁኔታ በህወኃት ካምፖች አካባቢ አለመረጋጋት መስፈኑ እውነት ነው" ሲል በመንፈስ ካልሆነ በስተቀር በምን ለማለት ስለሚያስደፍረን እኮ ነው ታምራት ገለታም ነው ተስፋዬ የምላችሁ፡፡ መች ይሂ ብቻ የተስፋዬ ታምራት ገለታነት ሌላም መገለጫ አለው። መፈንቅለ መንግሥት ይከሰታል የሚለው ትንቢቱ፡፡

ከሁሉ በላይ ግን የተስፋዬን ውሸት፣ የተስፋዬን አሉባልታ፣ የተስፋዬን ጉራ የሚያረጋግጥ ነገር በኃይለማርያም አንገት የመጨረሻው አንቀጽ ላይ ሰፍሮ አገኘሁት። ጉዳዩ ኃይለማርያም ደሳለኝን የተመለከተ ነው፡፡ "ጌታን የተቀበለ ሰው ስለሆነ፣ የኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ በላዩ ላይ አድሮ ኃይል ይሆነዋል" ብለው የነገሩኝ ሰዎች አሉ፡፡ ተስፋዬ ተአማኒነት ለሌላቸውና ተዓማኒ ሊሆኑ ቀርቶ ሊመስሉ ለማይችሉ ጉዳዮቹ ሁሌም ሁለተኛ ወገን ይፈልግላቸዋል፡፡ "የነገሩኝ" "የነገረኝ" የመሳሰሉትን ገፀ ባህርያት ይጠቀማል፡፡ ወደ ኋላ ተመልሼ ለዚህ "ለነገሩኝ" እና "ለነገረኝ" የተስፋዬ ማወናበጃዎች ጥቂት ማሳያዎች ላቀርብ፡፡

ቀደም ብዬ ለመጠቆም እንደሞከርኩት ተስፋዬ አንዴ ግለሰቦችን ሲሻው ደግሞ ብሄሮችን እና ብሄረሰቦችን አልሆንለት ሲለው ደግሞ ተቋማትን እና ባለሥልጣናትን በመወረፍና ኋዳ ጎድኋዳውን ሳይቀር ልክ እንደሚያውቅና ቅርበቱ እንዳለው በማስመሰል ካልሆነለት ደግሞ እገሌ ነገረኝ እያለ ማቡካት ልማዱ ነው፡፡

የጋዜጠኛው ማስታወሻ ሲል በሰየመው መጽሐፉም ይህ ባህሪው ጎልቶ የወጣበትና ማንነቱ የታየበት በፈጠራ ሀሳቦች የታጨቀ ስለመሆኑ በርካቶቹ ተስፋዬን የሚያውቁትና ማስታወሻውን ያነበቡት ሁሉ ያረጋገጡት ሀቅ ነው፡፡

ጥቂት ማሳያ ስል በእኔ በኩል የምጠቅሰውም ከዚሁ ማስታወሻ ካለውና "እውነተኛ ታሪክ" በማስመሰል ከቀረበው መጽሐፉ ላይ ነው፡፡

ጉዳዮቹ የሚመለከቱት ኮሜዲያን ደረጀ ኃይሌን፣ የቀድሞውን ፕሬዚዳንት ነጋሶ ጊዳዳ፣ አለቃው የነበሩትን አቶ በረከት ስምዖንን እና አቦይ ስብሃትን ነው፡፡

በመሠረቱ እነዚህን አጀንዳዎች ተመልክተን ብቻ የተስፋዬን አወናባጅነት መረዳት ይቻለናል፡፡ ሆኖም ግን ከላይ በተስፋዬ በኩል የተወራላቸው ግለሰቦች በህይወት አሉና ሀቁን ማረጋገጥና መፍረድም ይቻላል፡፡ እኔ ግን ከእነዚህ የተስፋዬ ጥቂምታዎች ጋር ተያይዞ አንድ አጋጣሚ ተፈጥሮልኝ ነበርና የተስፋዬን ጉዳ ጉድ ለእናንተም እንካችሁ ብያለሁ፡፡

ባልንጀራዬ አርቲስት ነው። ከኮሜዲያን ደረጀ ጋር ያለው ቅርበት ከእኔ ጋር ካለው ቅርበት ያልተናነሰ ነው፡፡ ከባልንጀራዬ ጋር ሰሞንኛውን የኢትዮጵያ ፖለቲካ በተመለከተ ሚዲያውን መሠረት አድርገን እያወጋን ነው፡፡ ተስፋዬ ገብረአብም የሰሞኑን አየር ተከትለው ከሚፈተፍቱት ውስጥ አንዱ ነውና አነሳነው፡፡ ባልንጀራዬ የተስፋዬን ውሸታምነት እና ዘላባጅነት ለማስረዳት ብዙም አልተቸገረም፡፡ በጋዜጠኛው ማስታወሻ በተስፋዬ በኩል የቀረበውንና ኮሜዲያን ደረጀን የተመለከተውን "ደረጀ ነገረኝ" የሚለውን አጀንዳ አነሳልኝ፡፡ እናም አለኝ "ተስፋዬና ደረጀ ተገናኝተው አይደለም አይቶትም እንደማያውቅ ደረጀ ነግሮኛል" ሲል የተስፋዬን ቀሽምነት አረጋገጠልኝ፡፡

ተስፋዬ በመሠረቱ ጋዜጠኛ ሆኖ የጋዜጠኛው ማስታወሻ ሲል ባስነበበን መጽሐፉ ፍፁም የጋዜጠኝነት ሥነ ምግባር የጎደለው እንደሆነና የወትዋችነት ሚናው አብሮት እንዳደገ ራሱም ያረጋግጥልናል። በየትኛው የጋዜጠኝነት መርህና ፍልስፍና ይሆን ለቃለ መጠይቅ ከእንግዳው ፊት ለፊት ተቀምጦ ተጠያቂው ዞር ሲል የተጠያቂውን አጀንዳ ገልጾ ማንበብ የተፈቀደው፡፡ "አቦይ ስብሃት ወጣ ሲሉልኝ ጠረጴዛቸው ላይ ያለውን አጀንዳ ገለጽ አደረግሁት..." ስለሆነም አቦይን ያዋረደ መስሎት ተስፋዬ የራሱን እርኩሰት ገልፆልናል፡፡ ተስፋዬ ሰላይና ወሽካታ እንጂ ጋዜጠኛ እንዳልሆነም ከራሱና አቦይን ከተመለከተው ማስታወሻው ማረጋገጥ ይቻለናል፡፡ የአቶ በረከትና የዶክተር ነጋሶን የተመለከቱትም ቢሆኑ የማይመስሉ፤ የተስፋዬ የግል ጥላቻ የተንፀባረቀባቸው፤ የማይጨበጡ እና ተዓማኒነት የሚጎድላቸው ፊልም መሰል ትርክቶች ቢሆኑ እንጂ እንደማስታወሻ ሊጠቀሱ የሚችሉ ነገሮች አይደሉም፡፡

ይኼ ግለሰብ ነው እንግዲህ ከነገረ ሽግግር መንግሥቱ ጀምሮ እስከ አሁንም ድረስ ለማደፍረስና ወሬ ለማናፈስ ሳይተኛ ማደሩን የተያያዘው፡፡ ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባም ቢሉም አበው ለተስፋዬ የመስከረም መጥባትና አለመጥባት ጉዳዩ አይደለም። በተገኘው ቀዳዳ ሁሉ መግባት እንጀራው ነው፡፡ ስለሆነም ኃይለማርያምን የእግዚአብሔር ኃይል ይረዳዋል ሲል ሰው ነግሮኛል ብሎ ሰውዬውን ባዶ ለማድረግ

ይሞክራል፡፡ ካልሆነም ሲል ደግሞ "በአቅም ማነስ" ወይም "በመፈንቅለ መንግሥት" መውረድ እጣ ፈንታው ነው ሲል ይለፍፋል፡፡

የሚኒልክን ወንበር ላይ አሁን ተቀምጦ ያለው ደርግ ይመስል ስለቀዩ ወንበርና ሰለባዎቹ በማውራት ለአቶ ኃይለማርያም ማስጠንቀቂያ በመስጠትም የማይገናኙ ነገሮችን በማገናኘት ለማምታታት ይሞክራል፡፡ ለዚህ ዓይነት ሰበካና ጂኒ ቁልቋል ደግሞ የኒዮ ሊበራሉ ኃይል የሚዲያ ፍልስፍናና አፈፃፀም ይመቻል፡፡ ስለተመቸውም ተስፋዬ ይቀባጥራል፡፡ ኒዮ ሊበራሉም ድረ ገጹን ለተስፋዬ ዓይነቶቹ ክፍት ያደርጋል፡፡ ለምን? የሚለው ጉዳይ ላይ ወደ ኋላ እመለስበታለሁ፡፡

ከዚሁ ከተስፋዬ ዲስኩር ጋር ተያይዞ ባለፈው መጣጥፌ የተመስገን ደሳለኝን ቂልነትም ማውሳቴ አይዘነጋም። ቂልነታቸውን የነገርኳቸው ተመስገንና ጋሻ ጃግሬዎቹ ደግሞ የባሰ አታምጣ እንዳሉ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ የተመስገን አድናቂ ናቸው ሲሉ ጅል ሆነውብኛል፡፡ ይህንንም ያስነበበን ያው የኒዮ ሊበራሉ ሚዲያ ከሆኑት ውስጥ አንዱ የሆነው ድረ ገጽ ሲሆን የጽሁፉ ባለቤትና ምንጮቹ ግን አይታወቁም፡፡

ባለፈው መጣጥፌ እና ለተመስገን ትርክት በሰጠሁት ምላሽ የተጋለጡትና የደነገጡት እነ ተመስገንና ጓዶቻቸው በበቂ ማስረጃ የቀረበውን እና የኢትዮጵያን ወቅታዊ ሁኔታ የተመለከተውን የግሌ አስተያየት ከመንግሥት የተሰነዘረ መስሏቸው ነው መሰል ሀሳቤን በሀሳብ ሊሞግቱ ሲገባ "ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ በፕሮፖጋንዳ ሠራተኞቻቸው ተበሳጭተው እንደነበር ምንጮች ገለፁ" የሚል መያዣና መጨበጫ የሌለው ዕሑፍ ፖስት አደረጉልኝ፡፡ ጠቅላይ ሚሚስትሩ አቶ በረከትን "ካንተ ሠራተኞች ያ ጋዜጠኛ ይሻላል" ሲሉ ተቆጥተዋቸው እንደነበርና ጠቅላይ ሚኒስተሩ ያ ጋዜጠኛ ያሉትም ተመስገን ደሳለኝን እንደሆነ ምንጮች ነግረውናል" ሲሉም የጅልነታቸውን ጥግ አሳይተውናል፡፡

ማን ፀሐፊ ማን ምንጭ እንደሆነ ምንም ፍንጭ የሌለው ይህ ፅሑፍ ትክክለኛና ጥሩ የኢ-ፕሮፌሽናሊዝም ማረጋገጫና የኒዮ ሊበራሉ ኃይል ፍልስፍና ማሳያ ሲሆን ተዋናዩቹም የዜሮ ድምር ፖለቲካ ሰለባዎች እንደሆኑ የሚያረጋግጥ ነው፡፡

ወጣም ወረደ እዚያም ተሄደ እዚህ፤ በጋዜጣም ተፃፈ በድረ ገፅ ኢህአዴግ ሂርቱን ሁሉ አልፎ በጉዞ ላይ ይገኛል፡፡ ኃይለማርያምም ወንበሩን ተረክቦ በማስፈፀም ሂደት ላይ ይገኛል፡፡ ግን ግን የእነዚህ ኃይሎች ፍላጎትና ተስፋ ምንድነው? ከኒዮ ሊበራሉ ኃይልስ ጋር ምን ያገናኛቸዋል? የሚለውን ማየት የበለጠ ነገሮችን ለማወቅ ያግዘናልና ከእነ ተስፋዬና ተመስገን ጋር ተያያዥ የሆኑትን የኒዬ ሊበራሉን የሚዲያ ፍልስፍና ብቻ ከብዙ በጥቂቱ እንመልከት፡-

የሚዲያ ኢንዱስትሪውን ፕሮፌሽናሎች በግራ ዘመም ኃይልነት እያስፈሩሩ የትልልቁን ባለሀብትና የቀኝ ክንፍ ፖለቲከኞችን አጀንዳ እንዲያራምዱ የማድረግ ጉዳይ በዓላማችን ኒዮ ሊበራሊዝም ከተንሰራፋበት ካለፉት 30 እና 40 ዓመታት ወዲህ ግልጽ ርዕዮተ ዓለማዊ ቅኝት ይዞ ሲሄድ ቆይቷል፡፡

የኒዮ ሊበራሊዝም ዋነኛ ግብ የኅብረተሰብን ሀብት በልዩ ልዩ ሽፋን ወደ ትልልቆቹ ባለሀብቶች ማሸጋገር ነው፡፡ እነዚህን ከፍተኛ ባለሀብቶችና የርዕዮቱ አቀንቃኞች አስተሳሰባቸው ወደ ተግባር እንዳይቀየር ከሚታገዷቸው ጉዳዮች መካከል የተደራጁ ብዙኃንና የሕዝብን ጥቅሞች ሊያስከብር የሚችል በሕዝብ የተመረጠ ጠንካራ መንግሥት መኖር ናቸው፡፡

ከዚህ በመነሳት ኒዮ ሊበራሊዝም መንግሥትን ማዳከምና የኅብረተሰብን የተደራጀ ሀልውና ማጥፋት ዋነኛ ርዕዮተ ዓለማዊ ቅኝቱ እንዲሆን አደረገ፡፡ ይህ በበለፀገው ዓለም ብቻ ላይ ሳይወሰን በመላው ዓለምም ተግባራዊ መሆን ያለበት አማራጭ የለሽ ርዕዮተ ዓለም ተደርጎ ተገፋበት። የምዕራቡ ዓለም ፖለቲካ በዋነኛነት በኒዮ ሊበራል ጥቅሞችና ርዕዮተ ዓለም የበላይነት ስር በወደቀበት በዚህ ዘመን ሌሎች አማራጮች ሁሉ በታቀደ አኳኋን ተዘመተባቸው፡፡ የሚዲያ ኢንዱስትሪው በሲቪል ማኅበረሰብ ንቅናቄ ሽፋን ከተደራጁት ኒዮ ሊበራል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር እጅና ጓንት ሆኖ የገበያ አክራሪነት ርዕዮተ ዓለም ዋና አራማጅ ሆነ፡፡ ኒዮ ሊበራልዝምን የማይሰብክ፣ በኒዮ ሊበራሊዝም ርዕዮት የማይምል የማይገዘት ጋዜጠኛም ሆነ አርታኢ በዋና ዋናዎቹ ሚዲያዎች ውስጥ በአብዛኛው የሥራ እድል የማያገኝበት ሁኔታ ተፈጠረ፡፡ ስለዚህም የፕሮፌሽናል ጋዜጠኛ ሠራዊት አባል የሆነ አብዛኛው ጋዜጠኛ ወደደም ጠላ ኒዮ ሊበራል ፖለቲካን ሊያራምድ ተገደደ።

ከዚህ በመነሳት ዓለም አቀፉ የኒዮ ሊበራል ሚዲያ የበለፀገው ዓለም መንግሥታት ለሕዝብ ተጠያቂ እንዲሆኑና በኅብረተሰብ ላይ አመጽም ሆነ ማንኛውንም የሥልጣን ብልግና እንዳይፈጽሙ ለመቆጣጠር ፍላጎቱም ዝግጁነቱም እንደሌለው ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ርዕዮቱ ኅብረተሰብን የባለሀብቱ መሣሪያ ለማድረግ እስካገዘ ድረስ የሀሰት መረጃዎችን በማቅረብ ወይም ከፊል እውነታዎችን ሙሉ እውነት አስመስሎ በማምታታት የሕዝብን የትኩረት አቅጣጫ ለማሳት እስከመንቀሳቀስ ይደርሳል፡፡

ኅብረተሰብን በሀሰት መረጃዎች ወይም ሆነ ተብለው በሚጎሉ ወይም በሚደፈቁ መረጃዎች ማደናገር ቀደም ሲል ኒዮ ሊበራል የገበያ ሥርዓቱ የተሻለ ምጣኔ ሀብታዊ ሁኔታ ላይ በነበረበት ወቅት የታየ ብቻ ሳይሆን አሁን በምንገኝበትና ኒዮ ሊበራሊዝም ከፍተኛ ቀውስ ውስጥ በተዘፈቀበት ጊዜ አሁን ላይም እንደቀጠለ ነው፡፡

በኒዮ ሊበራል ዓለም አቀፋዊ የሚዲያ የኮሚኒኬሽን ኢንዱስትሪውና በአፍሪካ መካከል ያለው ግንኙነትም መነሻና መድረሻ የምዕራቡ ዓለም መንግሥታትና ኩባንያዎች የፖለቲካ ኢኮኖሚ ጥቅሞች ናቸው፡፡ የምዕራቡ ዓለም ከአፍሪካ ጋር የመሰረተው ግንኙነት በተለያዩ ደረጃዎችና ምዕራፎች ያለፈ ከመሆኑም በላይ ለአፍሪካ ድቀትና ኋላ ቀርነት የበኩሉን አስተዋፅኦ ያበረከተ ነው፡፡

በዓለማችን የኒዮ ሊበራል መነሻና መድረሻ የኒዮ ሊበራል የፖለሪካ ኢኮኖሚ ማስፋፋት በሆነበት በዚህ ዘመን ኢትዮጵያ እንደማንኛውም አፍሪካዊ አገር አስተሳሰቡን በግድ እንድትጋት ለማድረግ የተካሄደባትን ጫና በመቋቋም የራሷን ነፃ መንገድ ከመምረጧ ጋር ተያይዞ የኒዮ ሊበራል ሚዲያና ኮሙዩኒኬሽን ሥርዓቱ የፕሮፖጋንዳ ሰለባ እስከመሆን ደርሳለች፡፡

ሰሞንኛውን ሠላማዊ የሆነ የሥልጣን ሽግግር ተንተርሶም ኒዮ ሊበራሉ ኃይል ፈረሶቹን እና ሚዳውን በመጠቀም በማያገባው እየገባ ያልበላውን እያከከና እየፈተፈተ ይገኛል፡፡ የራሱን ጥቅሞች ታሳቢ ያደረጉ የፖለቲካ ትንታኔዎችን እና የሹመት መደላድሎችን እስከማዘጋጀት የዘለቀ ሀሳቦችን በየድረ ገጹና መፅሔቱ በማስተጋባት ላይ ነው፡፡ ይህ እንዲሆንለት ካለው ቁርጠኛ ፍላጎት በመነሳት ደግሞ እኔ ያልኩት ካልሆነና ምክሬንም ኢህአዴጎች ካልተቀበሉት መጪው ጊዜ ፈታኝና የትርምስ ይሆናል በማለት በተለመደው የኒዮ ሊበራል ማቀንቀኛ ዘዴው ሕዝብን ከሥጋት ላይ ለመጣል ይሞክራል፡፡

የሀሰት መረጃዎች ከመፈብረክ ጀምሮ ጥቂት የሰማት ወሬ ላይ ሀሳብ በመጨመር ወይም "ሀ" ን ከሰማ እስከ "ሆ" በመቀጠል ነገር መደባለቅና በማምታታት ርዕዮቱን ለማስፈፀም የማይፈነቅለው ድንጋይ የለም፡፡

እነ ተስፋዬን እና ተመስገንን የመሰሉ ግለሰቦች ደግሞ ለርዕዮቱ አቀንቃኞች የተመቹ ናቸው፡፡ እነዚህ ኃይሎች ስለ ነፃ ፕሬስ የሚታገሉ በማስመሰል ስለግለሰቦች ነፃነት በመደስኮርና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መደለያ አዋርድ በመሸለም ግለሰቦቹን በነፃ ጋዜጠኝነት ስም እንዳሻቸው ይጋልቧቸዋል፡፡

ስለሆነም ነው እኮ እነ ተመስገን ባልነበሩበት ቦታ ላይ ሆነው ለማውራት የሚደፍሩት፤ ያልተፈጠሩበትን ዘመን ፖለቲካም ለማወራረድ የሚሹት፤ በኢትዮጵያዊነት ሽፋን በትምክህት ውስጥ ተዘፍቀው የሚገኙት፤ ተስፋዬ እና ተመስገንን መሰል አውደልዳይ "ጋዜጠኞች" ጫፍ ይዘው ቢቀጥሉም፤ ጠርዙን ይዘው ቢያሰፉም ወሬ ቢነግሯቸው ሀሳብ ቢጨምሩም አሁን በሀገራችን ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መስመር ከማይናወጥ መሠረት ላይ ቆሟል፡፡ የመሥመሩ ተዋንያኖችም ዳግም ቃል ኪዳናቸውን ለመሪያቸው በነበራቸው ፍቅርና ታማኝነት ላይ አድሰዋል፡፡ የተደረገው ሠላማዊ የሥልጣን መተካካተም የአዲሱቷን ኢትዮጵያ መፃኢ እድል አመላክቷቸዋል፡፡ ለወሬኞች የሚሆን ጆሮ ያለው ኅብረተሰብ ዛሬ በኢትዮጵያ ማግኘት ከባድ ይመስለኛል፡፡ እዚያው በፀበላችሁ። ከኒዮ ሊበራሉ ጉድጓድ ተንቦራጨቁበት፡፡ እኛ በሥራ ላይ ነን፡፡ በህዳሴ ግድብ ግንባታ ላይ ነን፤ የእድገት እና የትራንስፎርሜሽን እቅድ በማስፈፀም ሂደት ላይ ነን፤ በመሠረተ ልማት ግንባታ ላይ ነን። አዲዮስ።